የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No. 36
Addis Ababa 17th July, 2022

**ማውጫ**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ማሻሻያ አዋጅ**

ገፅ……………………………………………፲፱፻፹፰

## አዋጅ ቁጥር ፸፰/፳፻፲፬

## የአዲሰ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ማሻሻያ አዋጅ

እጅግ ወሳኝና አጣዳፊ ወይም ልዩ ባህሪ ያላቸው እንዲሁም ለነዋሪው ሕዝብ ያላቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የጎላ ግዥዎች በልዩ ሁኔታ ስለሚፈጸሙበት ሁኔታ በህግ በግልጽ መደንገግ በማስፈለጉ ፤

የከተማው አስተዳደር የመንግስትና የግል አጋርነት የሚመሠረትበት ሁኔታ እና ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ እንዲወሰን ማድረግ አስፈላግነቱ ስለታመነበት፤

ለዚህም ስራ ላይ ያለውን የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

የአንዱ ዋጋ
Unit price

**Addis Ababa City Government Procurement and Property Administration Amendment Proclamation**

**Page ……… 1988**

## Proclamation No. 78/2022

## ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT PROCUREMENT AND PROPERTY ADMINSTRATION AMENDMENT PROCLAMATION

WHEREAS, it is found necessary to clearly regulate by law about the special conditions of procurements that are very important, urgent or special in nature and have social and economic importance for the resident population;

WHEREAS, the Addis Ababa City Government it is believed the necessary to establish the situation and detailed implementation of the public-private partnership;

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፰
Addis Negari Gazeta P.O.Box

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ረ) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህንን ማሻሻያ አዋጅ አውጥቷል ፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ " የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዥና የንብረት አስተዳደር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፸፰/፪ሺ፲፬ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ማሻሻያ</u>**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፲፯/፪ሺ፪ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩. የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፳፯) እና (፳፰) ተሽረው በሚከተለው አዲስ ንዑስ (፳፯) እና (፳፰) ተተክተዋል፤

"፳፯. **"የመንግሥትና የግል አጋርነት"** ማለት በተዋዋይ ባለሥልጣን እና በግል ባለሀብት መካከል የሚደረግ ስምምነት ሲሆን ይህም ስምምነት የግል ባለሀብቱ፡-

ሀ) በተዋዋይ ባለሥልጣን ሊካሄድ ይችል የነበረን የሕዝብ አገልግሎት ሥራ ለማከናወን የውል ግዴታ የሚገባበት፤

NOW, THEREFORE, in accordance with letter (f) of sub-Article (1) Article 14 of the Revised Charter of Addis Ababa City Government Proclamation No. 361/2003 (as amended) the Addis Ababa City Council has issued this amendment proclamation as follows.

**1. <u>Short Title</u>**

This proclamation may be cited as «The Addis Ababa City Government Procurement and property Administration Amendment Proclamation No.78/2022».

**2. <u>Amendment</u>**

The Addis /2009 is hereby amended as follows: Ababa City Government Procurement and property Administration Proclamation No.17

1. Sub-Article (27) and (28) of Article 2 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (27) and (28).

**"27. "Public Private Partnership"** or **"PPP"** means an agreement made between a contracting authority and a private investor under which the private investor shall:

A. enters an agreement to perform a public service activity that could have been carried out by the contracting authority;

ለ) በሚከተለው አኳኋን ጥቅም የሚያገኝበት እና ኃላፊነት የሚወስድበት ነው፡-

፩) በተዋዋይ ባለሥልጣን ወይም ስለተዋዋይ አካል ሆኖ የተፈፀመን ክፍያ ፤

፪) ከአገልግሎት ተጠቃሚዎች ወይም ደንበኞች በታሪፍ ወይም በክፍያ መልክ የሚሰበሰብ ገንዘብ፤ እና

፫) እነዚህን ታሪፎች ወይም ክፍያዎች በጣምራ፤

ሐ) በፕሮጀክት ስምምነት መሠረት ከሥራው እንቅስቃሴ ወይም በመንግሥት ንብረት ከመጠቀም ጋር ለተያያዙ ሥጋቶች ኃላፊነት የሚወስድበት ነው፡፡

"፳፰. **"ተዋዋይ ባለሥልጣን"** ማለት ከግል ባለሀብት ጋር የመንግሥት እና የግል አጋርነት ስምምነት ለማድረግ የሚፈልግ የከተማው አስተዳደር የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው፡፡"

፪. የአዋጁ አንቀጽ ፳፮ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፳፮ ተተክቷል ፤

"**፳፮. <u>የመንግስት እና የግል አጋርነት</u>**

የመንግስት እና የግል አጋርነት የሚመሰረትበት ሁኔታ እና አፈጻጸም የከተማው ካቢኔ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል ፡፡"

B. benefit out of it and take responsibility through the following conditions:

1. payments made by the contracting authority or on behalf of the contracting entity;
2. tariffs or fees collected from users or customers of a service;
3. a combination of such tariffs or fees;

C. take responsibility for risks arising from the activities of the work or the utilization of public property as per the terms of the project agreement;

**28 "Contracting Authority"** means a public office or public enterprise that intends to enter into a public private partnership agreement with a private investor;"

2. Article 26 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 26.

**"26. Public Private partnership**

The City cabinet may issue regulation prescribing the rules governing the formation of public private partnership and the modes of implementation of such partnership. ."

፫. ከአዋጁ አንቀጽ ፳፭ ንዑስ አንቀጽ (፬) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተጨምሯል ፤

"፭. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፭) የተደነገገው ቢኖርም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተፈቀዱ መደበኛ የግዥ ዘዴዎች ውጪ ከተማ አቀፍ ፋይዳ ያለው፤ እጅግ ወሳኝና አጣዳፊ ወይም ልዩ ባህሪይ ኖሮት ለነዋሪው ሕዝብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ ምክንያት ግዥ እንዲፈጸም ካቢኔው ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡"

፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከ ሐምሌ ፲ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፲ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

3. The following new Sub-Article (5) is added following Sub-Article (4) of Article 25 of the Proclamation.

" **5.** Notwithstanding the provisions of Article 12 Sub-Clause (5) of this proclamation, which has a city-wide value other than the normal procurement methods allowed in Sub-Clause (1) of this Article; The Cabinet may give an order to carry out a purchase due to the fact that it has a very important, urgent or special character and is of great social and economic importance to the resident population. The detailed implementation will be determined by the Cabinet's regulations."

**3. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force as of this 17th day of July 2022.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of July 2022.**

**Adanech Abiebie**

**Mayor of Addis Ababa City**